# የአማራ ፋኖ ድምፅ
# The Voice of Fano

በወቅታዊ አርዕስት በአፋሕድ የፖለቲካ ጉዳዮች መምሪያ እየተዘጋጀ የሚቀርብ
Issued by AFPO Department of Political Affairs on Current Topics
ጽሁፍ ለመላክ → contributions@thevoiceoffano.com ← for contributions

Vol. 1; No. 5
አንደኛ ዓመት አምስተኛ እትም

Wednesday, September 17, 2025
ረቡዕ መስከረም ፯ ቀን ፳፻፲፰ ዓ.ም.
https://thevoiceoffano.com


## ርዕሰ አንቀጽ

### አማራ እንደ ፖለቲካ ማኅበረሰብ ሲገመገም (ከባለፈው ሳምንት የቀጠለ)

**1. አማራ እንደ ፖለቲካ ማኅበረሰብ ምን ደረጃ ላይ ይገኛል?**

የአማራ ሕዝብ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ተሳትፎ ውስጥ ትልቅ ድርሻ ያለው ሕዝብ ነው። ሀገርን ከጠላት መከላከል፣ ሀገር ሰላም በሆነ ጊዜ በደረሰበት የኢትዮጵያ ቦታ ሁሉ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር ተዋሕዶ እና ተስማምቶ ለረጅም ዘመን የኖረ ሕዝብ ነው። በዚህ ሂደት ውስጥ ከሌሎች ሕዝቦች ጋር በስልተ-ምርት፣ በቋንቋ፣ በጋብቻ በእምነት እና በሌሎች የማኅበረሰብ መስተጋብር ተሳስሮ ለሀገር አንድነት የጎላ ሚና ተጫውቷል። ይህን የሀገር ዋልታና ማገር የሆነ ሕዝብ በጠላትነት በመፈረጅ ለሀገር አንድነት ጸር በሆነ የፖለቲካ አቋም፤ አንዳንዶች በስሜት፣ አንዳንዶች ደግሞ በተጠና መልኩ ሀገርን ለማፍረስ ከውጭ ከነ አሰስ ገሰሱ ያስገቡት የ1960ዎቹ ትውልድ ለአማራ ሕዝብ እና ለኢትዮጵያ ከፍተኛ የሆነ የፖለቲካ ቀውስ ጉዞ የጀመሩበት ጊዜ ነበር።

ከሁሉም በተለየ መንገድ የኢትዮጵያ የተማሪዎች ንቅናቄ የአማራን ሕዝብ በጨቋኝነት በመፈረጅ ሌሎች ብሔር ብሔረሰቦች ጭቁን መሆናቸውን ቀስ በቀስ እያስተማረ እና እያጠናከረ ሂዶ በመጨረሻም የአማራ ተወላጆችን በልቷል። የተማሪዎች ንቅናቄ በርካታ ኢትዮጵያውያን የተሳተፉበት ሲሆን በተለይ ደግሞ የኤርትራ፣ የትግራይ፣ የኦሮሞ እና የአማራ ተወላጆች ትልቁን ድርሻ ይወስዳሉ። የተማሪዎችን ንቅናቄ በፊትአውራሪነት ሲመሩት የነበሩት በውስጣቸው ኢትዮጵያን አምርረው ይጠሉ የነበሩ ኤርትራውያን እና ህወሓታውያን ነበሩ።

ከአማራ ተወላጆች ውጭ ያሉት ሁሉም የተማሪዎች ንቅናቄ ተሳታፊዎች ከጀርባቸው ተልዕኮ ያነገበ ሌላ ድርጅት ስለነበራቸው ከትግራይ የመጡት የተማሪዎች ንቅናቄ አባላት ከህወኃት፣ ከኤርትራ የመጡት ደግሞ ከሻዕቢያ እንዲሁም ኦሮሞዎች ደግሞ ከኦነግ ጋር አብረው ይሰሩ ነበር። በተቃራኒው ግን የአማራ ተወላጆች የወቅቱን የፖለቲካ ነባራዊ ሁኔታ በአግባቡ ባለመረዳታቸው እና ከብስለት ማነስ በመነጨ መልኩ ሀገርን ልክ እና ወሰን በሌለው የቅዠት ፍቅር ውስጥ በመግባታቸው ራሳቸውን ሊከላከሉበት የሚችል ሌላ እቅድ አለነበራቸውም። ደርግ ስልጣን ይዞ የተማሪዎች ንቅናቄ ከፈረሰ በኋላ ከአማራ ውጭ ያሉት ሁሉም የተማሪዎች ንቅናቄ አባላት ጸረ-አማራና ፀረ-ኢትዮጵያ ወደ ሆነው ሌላኛው ጎሬአቸው ማለትም ወደ ህወኃት፣ ሻዕቢያ እና ኦነግ ሲገቡ የአማራ ተወላጆች ግን ወይ ተሰደዋል ወይም ተገድለዋል ወይንም ደግሞ በሌላ መንገድ ባክነው ቀርተዋል። በዚህም ምክያት የአማራ ሕዝብ የትውልድ ክፍተት (generation gap) ተፈጥሮበታል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አማራ ከፈተኛ ዋጋ ከፍሏል። ይህም የሆነው በወቅቱ የነበረውን የፖለቲካ አሰላለፍ፣ መርህ እና ነባራዊ ሁኔታ በአግባቡ ካልመረዳት የመነጨ ነው። የዚህ ሰነድ መሰረታዊ ቁምነገር፡ *የአማራ ልሂቅ ከዚያ ዘመን ታሪካዊ ስህተት ትምህርት ወስዶ አሁን ያለውን የኃይል አሰላለፍ መርምሮ የአማራ ሕዝብ በዘላቂነት ችግሩን የሚፈታበት አደረጃጀት መሥርቷል ወይንስ አሁንም ተመሳሳይ ስህተት ለመፈፀም አሰቧል የሚለው ነው።*

**2. አማራ የፖለቲካ ማኅበረሰብ ለመፍጠር የገጠመው ችግር**

የአማራ ሕዝብ የፖለቲካ ማኅበረሰብ እንዳይሆን ያጋጠሙትን ችግሮች ከውጫዊ እና ከውስጣዊ ሁኔታዎች አንጻር ማየት ያስፈልጋል። ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ነጥቦች ሕዝቡ የፖለቲካ ማኅበረሰብ እንዳይሆን እንቅፋት የሆኑ ናቸው።

**2.1. ለረጅም ዘመን የተሰራው የተጠና እና የገነገነ የውሸት ትርክት**

ኢትዮጵያ ጠል የሆኑት የህወኃት እና የኦነግ ፅንፈኛ ሀይሎች የአማራ ሕዝብን በጠላትነት እና በጨቋኝነት በሰፊው ፈርጀው በመሥራታቸው ቀሪውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሎም ዓለም-ዓቀፉን ማኅበረሰብ በተሳሳተ መንገድ ከነሱ ጎን እንዲሰለፍ ማድረግ ችለዋል። በዚህም ምክንያት በአማራ ሕዝብ ላይ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ዘር ጭፍጨፋ ሲካሄድ ማንም ትኩረት ሳይሰጠው ቆይቷል። አማራ ጨቋኝ ነው፣ አማራ ጨፍጫፊ ነው፣ ተመልሶ ወደ ስልጣን ከመጣ ሀገሪቱን በአንድ ቋንቂ እና በአንድ ሀይማኖት ጨፍልቆ ይገዛል የሚሉ እጅግ በጣም ከእውነታ የራቁ ትርክቶች የአማራ ሕዝብ ራሱን ችሎ እንዳይደራጅ፣ ቢደራጅም ጨፍላቂነት የሚለውን የሀሰት ክስ በመክሰስ ሕዝቡ ተሸማቆ እንዲኖር ተደርጓል። (ገጽ 2 ላይ ይቀጥላል።)




### ነፍጠኛ

ልኳትን በሰንደቅህ ስር ግርጌ፤
የፅዋ ደምክን ፈልጌ፤
ባክህ አባት ሆይ ሰማኝ ደምህ ሕዝብህን አደራ፤
ለሚደርሰበት ግርፋት ኢምንት ቁራጪን አልፍራ፤
የሞትም ፅዋ ካለበት ቀድሜ እኔ ልጠራ።
የመ'ና ቤት የለውም ባክህ መ'ና አታድርገኝ፤
ወይ መከራውን ልካፈል ከሰቀቀኑ ይድረሰኝ፤
በሕዝብህም ቃጠሎ በነበልባሉ ልማገድ፤
ከአካሉ ጋራ ልላተም ከእምነቱ ጋራ ልገመድ፤
ሰላሳ ሰድሳም ይቅርብኝ መቶንሰ እንኳ አልድፈር፤
ከመቅደሰ ግርጌው ልሙት ከፅላቱ ጋር ልሰበር።
ባክህ ጀግናዬ ሆይ ሰማኝ!!
በሰቀቀኑ ልሳቀቅ በቃጠሎው ልቃጠል፤
የጀርባው ቁስል ይድረሰኝ በቁስሉ ትሎች ልገንፍል፤
በጉጥ ጅራፉ ልገረፍ፤
ደሜ እንደ ደምህ ይንጠፍጠፍ፤
አልያ አባት ሆይ እባክህ በናትህ ምልጃ አትጨክን፤
ለትንሳኤው ልመረጥ መንገድ ጠራጊው ልሁን።
የጴጥሮስን ልብ ሰጠኝ እንዳልሸሽ ለጠላቶቹ፤
ጦሩን ከጎኑ ልምዘዘው ሰይፉን ከሁለት እጆቹ፤
እሳቱን በእሳት ላጥፋለት ከሚገረፉ ልጆቹ፤
በውሃ ጥሙ ልጠማ በርሃቡ የእንጨት ስር ልማሰ፤
ለመጫሚያው ኩርንችት ለእንቅልፉ ድንጋይ ልንተራስ።
እባክህ ጀግናዬ ሆይ አትራቀኝ!!
ለንሰሃው እብቃና ከጴጥሮሰ እምነት ላክልኝ፤
ለቃል ኪዳንህ ልሰዋ ለትንሳኤው ልጠራ፤
ለሚደርሰበት ግርፋት ኢምንት ነፍሴ እንዳትፈራ፤
እባክህ አባት ሆይ አደራ።

አሻግሬ ባየ የልብ ስንቅ፥ 2017 ዓ.ም
(መታሰቢያነቱ፤ ለሜጀር ጄኔራል ከፍያለው ደሴ ነው።)

## Editorial

### The Amhara as a Political Community (continued from last week)

**1. What is the Status of the Amhara as a Political Community?**

The Amhara people have played a significant role in Ethiopia's political landscape, contributing to national unity through coexistence, intermarriage, and shared cultural values with other ethnic groups. However, since the 1960s, the Amhara have faced a political crisis due to narratives propagated by certain groups, particularly during the Ethiopian Student Movement, which labeled the Amharas oppressors. (continued on Page 2)

### Notes on Pan Africanism

**Eskinder Nega, AFPO Chairperson.**

It is almost a cliché to point out that Africans are more connected to one another today than ever before, thanks to the proliferation of digital platforms. Who, in this age, could possibly deny such an obvious reality? Yet the deeper question remains: what has been the true impact of this digital revolution on Pan-Africanism itself? Has it strengthened the cause, diluted it, or left it stagnant despite the illusion of connectivity? These are not trivial questions. What we urgently need is a sober and comprehensive continental overview—an honest examination of whether our digital interconnections are merely superficial bonds or whether they are serving as genuine conduits for political consciousness, unity, and liberation.

To give credit where it is due, certain figures have already made deliberate use of these digital avenues to rekindle the spirit of Pan-Africanism. Professor P.L.O. Lumumba stands tall among them. Through his tireless advocacy, he has carried the torch of Pan-African unity into the digital age, delivering speeches that pierce through apathy and resonate with the restless energy of Generation Z. His fiery rhetoric, steeped in both historical awareness and contemporary urgency, has breathed new life into an ideal that too often risks being confined to academic debates or political rhetoric. While it may be true that this movement has yet to reach a critical mass, the seeds have undeniably been planted—and they are beginning to find fertile ground. That alone is a promising start. (to continue on Page 3)

### ተጨማሪ አርዕስት፤


- የሳምንቱ አበይት ዜናዎች (ገጽ 3)
- በምስሎች (ገጽ 5)


### More titles:


- Weekly News Update (Page 3)
- In Pictures (Page 5)

# የአማራ ፋኖ ድምፅ

Vol. 1; No. 5
አንደኛ ዓመት አምስተኛ እትም

አማራ እንደ ፖለቲካ ማኅበረሰብ ሲገመገም (ከገጽ ፤ የቀጠለ)

ከዚህም በላይ አዲሱን የአማራ ትውልድ በመነጠል በተለይም ወጣቱንና ተማሪዎች እውነተኛውን ታሪክ የተሳሳተ አስመስሎ በማቅረብ አዲስ የሀሰት ትርክት እንዲጫንባቸው በሰፊው ተሰርቷል። ልዩ ልዩ ህትመቶችን በገፍ በማባዛት፣ በሚዲያ በማሰራጨት፣ የሀሰት ምስክሮችን በምሁራ መልክ በታጋይ መልክ በሀገር ሽማግሌና የኃይማኖት አባቶች ሳይቀር ስሁት የሆነ ማብራሪያ እዲሰጡ በማድግ የአማራ ሕዝብ ላይ ከፍተኛ ደባ ተሰርቶበታል። የሀገርን ሉዓላዊነት ለማስከበር ከሁሉም የውጭ መራሪ አካላት ጋር ከፊት ቀድሞ በመፋለም ባቆየት ሀገር ነገሩ ወርቅ ላበደረ ጠጠር ሆኖ ራሱን በራሱ እንዲኮንን ለማድረግ እኩይ ሥራ ተሰርቶበታል። የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን በክረምት ወቅት በተለያዩ የማሰልጠኛ ጣቢያዎች ገብተው በእነ በረከት ስምን፣ መለስ ዜናዊ፣ አዲሱ ለገሰ፣ደመቀ መኮነን፣ ህላዊ ዮሴፍ፣ እና ቀንደኛ ጸረ-አማራ ቡድኖች በተዘጋጀ ጸረ-አማራ ሰነድ እንዲሰለጥኑ በማድረግ ከእውነት እንዲርቁ ለማድረግ ብዙ ሥራ ተሰርቷል።

### 2.2. ከሕዝቡ ስነ-ልቦና እና ነባራዊ ሁኔታ በእጅጉ በሚርቁ ሰዎች መወከሉ

ከላይ የጠቀስናቸው ፀረ-አማራ ሀይሎች ስልጣን ከያዙ እና ኢትዮጵያን ቋንቋን መሰረት ባደረገ (Ethno-linguistics) የፌደራል ሥርዓት ከመሰረቱ በኋላ የአማራ ሕዝብን እንዲመሩ የተመደቡ ግለሰቦች በስነ-ልቦና ከሕዝቡ ብዙ የራቁ፣ በሆዳቸው ብቻ የሚያስቡ በመሆናቸው ሕዝቡ እንዳይደራጅ፣ እንዳይነቃ እና እንዳይታገል ጨቁነውታል። ነባር ፀረ-አማራ ብአዴን ካድሬዎች በከፍተኛ ወንጀል የተጨማለቁ በመሆኑ ፀረ-አማራ ለሆኑ ድርጅቶች የህይወት ዘመን ታማኝ አገልጋይ ሆነው በአዲሱ ትውልድም አማራን እያስጨፈጨፉ ለመቀጠል የእነሱን ሃሳብ ተቀብለው ለሚያራምዱ በተለይም በትምህርታቸው ዝቅተኛ ውጤት ያላቸውን የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን አማራጭ መንገድ ነው ብለው በማሳሳት ለጸረ-አማራው ድርጅት ታማኝ ካድሬ እንዲሆኑ ተደርገው ተሰርቷል።

በክልልና በፌደራል ደረጃ የምናገኛቸውና ዛሬም ድረስ አማራን እያስጨፈጨፉ ያሉ ጉምቱ ባለስልጣናት በሆዳቸው አማራን ከደው ከፀረ-አማራ ድርጅትና አመራሮች ጋር አብረው ሲሰሩ የነበሩ ታማኝ ሎሌዎች ናቸው። የባንዳ ኔትወርካቸውን በቤተሰብና በጥቅም ተሳስረው እስከ ወረዳ ድረስ በማሰማራት አሁን ድረስ የነቁ አማራዎችን በማፈን ለአምባ ገነን ሥርዓት አገልጋይ ሆነው ቀጥለዋል። በዚህ እኩይ ሥራቸው የሕዝቡን የመደራጀት፣ የመታገል እና አማራጭ ሀሳብ የማቅረብ አቅሙን ገና ከእንጭጩ በመቅጨት ሲፈታተኑት ኖረዋል። ይህ ኔትወርክ በካድሬው ብቻ ሳይሆን ሀቀኛውን ነጋዴ በማጥፋት የሥርዓቱ አገልጋይ ነጋዴዎች፣ ለአገዛዙ ያደሩ የኃይማኖት አባቶች፣ በትምህርት ሴክተሩም እስከ ዩኒቨርሲቲ ድረስ ገብተው የካድሬ መፈልፈያ እንዲሆን አድርገዋል። መላ ሕዝቡ ፀጋውን ተጠቅሞ እንዳይለማ የሀሳብ ድረቀት የገጠማቸው፣ ጥላቻ ያለባቸው፣ የዘር ማጥፋት ወንጀል ሲፈጸም ያልሰሙ መስለው የሚያልፉ፣ የፖለቲካ ተገቢ ውክልና ሲጠየቅ ጽንፈኛ የሚል ስም መለጠፍ እና ሌሎችም የሕዝቡን ነባራዊ ሁኔታዎች ወደፊት እንዳይመጡ በመሸፋፈን ሕዝቡን በፖለቲካ ንቃተ-ህሊናው ደብዛዛ አድርገውታል።

ይህ ውስብስብ ሴራ የፖለቲካ ማኅበረሰብ እንዳይፈጠር ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። ይህ ሁኔታ አሁን ባለው የብልጽግና ሥርዓትም እጅግ በተጠናከረ እና በሰፊው እየተሰራበት ሲሆን በአደባባይ የሀገሪቱ መሪዎች ሕዝቡን በፈለጉት ቃላት እየሰደቡትና እያሸማቀቁት ይገኛሉ።

### 2.3. በአማራ ኃይሎች መካከል የሚፈጠር የእርስ በእርስ መገፋፋት

የአማራ ሕዝብን ዘረፈ-ብዙ ችግር ተገንዝበናል ብለው ሕዝቡን መነሻ አድርገው ወደ ትግል የገቡ ሀይሎች በጋራ ከመሥራት ይልቅ እርስ በርስ በመገፋፋት በየጊዜው የሚታይ የፖለቲካ ማኅበረሰብ እንዳይፈጠር ሌላኛው ችግር ነው። እነዚህ ሀይሎች ለአማራ ሕዝብ የሚጠቅመው "የዜግነት ፖለቲካ ወይም የብሔር ፖለቲካ" በሚለው ጉዳይ በርካታ ሀይል ከኋላቸው አሰልፈው የሕዝቡን አቅም በማዳከም ዋጋ አስከፍለውታል። ይህም በራሱ በልሂቃኑ ላይ ያለውን የፖለቲካ ንቃት ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ነው። የወቅቱን ቀጠናዊ እና ሀገራዊ ነባራዊ ሁኔታ በአግባቡ ተንትኖ አቅጣጫ በማስቀመጥ ጠቃሚውን መንገድ ለይቶ ማታገል ሲገባ እርስ በርስ መገፋፋት በግልጽ የሚታዩ ችግሮች ናቸው። በተመሳሳይ መልኩ የአማራ ሕዝብ ጥያቄዎች በምርጫም ሆነ በድርድር ሊፈቱ አይችሉም፣ በትጥቅ ትግል ብቻ ነው መፍትሄ የሚመጣው የሚለውን አቋም ይዘው ወደ ጫካ የገቡ ሀይሎችም እንኳ በአውራጃዊ እና በጎጥ አደረጃጀቶች ተከፋፍለው እርስ በርስ በመጓተት ሕዝቡ በአግባቡ እንዳይደራጅ፣ ጠንካራ አማራዊ ተቋም እዳይፈጠርና የዲፕሎማሲ ሥራውን አጠናክሮ ለመሥራት መጓተትን ፈጥረዋል።

### 2.4. በግለሰቦች ላይ የተንጠለጠለ ትግል ማራመድ

ትግል የተቋም ሥራ ነው። ትግል ውጤት እንዲያመጣ በህግ፣ በሰው ሀብት እና ለሕዝብ ቅርብ የሆነ ተቋም ያስፈልገዋል። በአማራ ሕዝብ ውስጥ የሚደረጉ ትግሎች ግለሰብን የማምለክ ሁኔታ በብዛት ይስተዋላል። ግለሰቡ ካለፈ ወይም ከትግል ከወጣ ትግሉ ይቆማል ማለት ነው። ነገሩን እጅግ ውስብስብ ያደረገው ደግሞ ግለሰቦች በአማራነታቸው ላይ ባላቸው አቋም ሳይሆን በሰፈር፣ በወረዳ እና በክፈለ ሀገር ሳይቀር የምንመካበት መሆኑ ነው። ይህ አካሄድ በምንም አይነት መልኩ የፖለቲካ ማኅበርሰብ ሊፈጥር አይችልም፣ እንቅፋት ነው። ስለሆነም አማራን የፖለቲካ ማኅበረሰብ ማድረግ ከተፈለገ ትግሉን ከግለሰቦች እጅ ፈልቅቆ በማውጣት ጠንካራ ተቋም ሠርቶ ትግሉን የሕዝብ ማድረግ ያስፈልጋል። ሕዝብን ታች ድረስ ወርዶ ለማንቃት፣ ለማደራጀት እና ለማታገል ከግለሰብ ይልቅ አማራዊ ተቋም ፋይዳው የጎላ ነው።

### 2.5. ያልተጠና ጀብደኝነት

የአማራ ሕዝብ ስሜቱን፣ ባህሉን፣ ሀብቱን እና ጥንካሬውን የሚገልጽበት የራሱ የሆነ እሴት ያለው ሕዝብ ነው። ነገር ግን ብዙ ጊዜ ለፖለቲካ እና ለሌሎች ማኅበራዊ ሥራዎቻችን መጠቀም ያለብንን መለየት አለመቻላችን ሕዝቡን ለውስብስ ሁኔታ ዳርጎታል። እኔ




ገጽ 4 ላይ ሙሉ ዜናውን ይመልከቱ።

የቴዎድሮስ ልጅ፣ የበላይ ልጅ፣ የምንይልክ ልጅ እያልን በመፎከር አማራን ነጻ ልናወጣው አንችልም። እንደ አባቶቻችን እቅድ በማቀድ፣ ወቅታዊ ሁኔታውን በመረዳት፣ ስትራቴጂክ ሥራዎችን በመሥራት እንጂ በፉከራ የሚመጣ ነፃነት ወይንም የሚድን ሕዝብ እንድሌለ አስምሮ መሄድ ያስፈልጋል። ይህ ፉከራ ከስሜት ያለፈ ሚና ስለሌለው የፖለቲካ ማኅበረሰብ ለመፍጠር ተጨባጭ የሆነ ሥራ በመሥራት ብቻ የሚመጣ ነው። ስለዚህ ያልተጠና ጀብደኝነት ሕዝቡን እንደ ሕዝብ እንዳይደራጅ ከማድረጉም በላይ ትክክለኛ ግምገማ እንዳይኖር በማድረግ ለውድቀት የሚዳርግ ነው።

## 3. የፖለቲካ ማኅበረሰብ ለመፍጠር ምን መደረግ አለበት?

### 3.1. የአማራን ሕዝብ ታሪክ በአግባቡ ማጥናት እና መሰነድ

የአማራ ሕዝብ በጨቋኝነት እና በበዝባዥነት በመወንጀሉ ለበርካታ ችግሮች ተዳርጓል። እነዚህ ፀረ-አማራ ትርክቶች ከየት እንደጀመሩ፣ እንዴት እንደበሰሉ እና እንዴት ፍሬ እንዳፈሩ በአግባቡ በማጥናት፣ መሰነድ እና ለትውልድ ማስቀመጥ ያስፈልጋል። ይህ የሚደረገው የአማራን ሕዝብ ቂመኛ ለማድረግ ሳይሆን የደረሱበትን ግፎች በመረጃ አስደግፎ ለመሞገት፣ የህቡን ጥቅም ለማስከበር እና ትውልድ ከበፊቱ ስህተት መማር እንዲችል ትልቅ አስተዋጾ ስላለው ነው። በተጨማሪም ጸረ-አማራ እና ጸረ-ኢትዮጵያ ሀይሎችም ሀገራቸውን እንዴት በውሸት ሲያስተዳድሩ እንደነበር እና እንዲህ አይነት ሥርዓት ወደፊት እንዳይመጣ የራሱ አስተዋጾ ይኖረዋል። አንድ ምሳሌ ለማንሳት አማራ ጨቋኝ እና በበፊቶቹ ሥርዓቶች ተጠቃሚ ነበር ብለው የውሸት ትርክት ያቀረቡት ፀረ-አማራ ድርጅቶች እ.ኢ.አ በ 1991 በኮንግረስ ላይበረሪ ተጠንቶ የታተመውን (Ethiopia: a country study) ጥናት ወለጋ፣ ትግራይ፣ ሀረርጌ፣ እና ሌሎች አካባቢዎች ከጎንደር፣ ጎጃም፣ ወሎና ሸዋ በትምህርት ቤት ስርጭት፣ በሀኪሞች ብዛት፣ በጤና ተቋማት ብዛት በእጅጉ እንደሚበልጡ በዝርዝር አስቀምጧል። ስለዚህ ጠንካራ የፖለቲካ ማኅበርሰብ ለመፍጠር የሕዝቡን ታሪክ፣ የፖለቲካ ሁኔታ፣ የተሰሩ የውሸት ትርክቶችን እና እሴቱን በአግባቡ በማጥናት እና በመሰነድ ማስተማር ያስፈልጋል።

### 3.2. ተቋማዊ ትግልን መለማመድ እና ማሳደግ

ትክክለኛ የፖለቲካ ማኅበረሰብ የሚፈጠረው በተቋማዊ አሰራር ነው። የማይናወጥ፣ ወጥነት ያለው እና ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን መረዳት የሚችል የፖለቲካ ማኅበረሰብ የሚፈጠረው በተቋም አማካኝነት ነው። ይህም በሁለት መልኩ የሚሰራ ሲሆን ከታች ወደ ላይ የሕዝቡን ጠቃሚ እሴቶች በመልቀም ተቋማዊ ቅርጽ ማስያዝ እና እንደ አማራ ሕዝብ ተመሳሳይ ግፍ በትግል የቀለበሱ ሀገሮችን ተሞክሮ በጥንቃቄ በማጥናት ወደ እኛ ነባራዊ ሁኔታ ማጣጣምና ሥራ ላይ ማዋል ይቻላል። በዚህ መልኩ ተቋም በመገንባት ጠንካራ የሆነ የፖለቲካ ማኅበረሰብ መፍጠር ይቻላል።

### 3.3. ልሂቁን ከቅዠት የማውጣት አስፈላጊነት

የአማራ ልሂቃን ሀገር በዜግነት ፖለቲካ እንድትመራ ያላቸውን ሀሳብ ባያሳውቁም የብሔር ፌደራሊዝም ፋሽን የሆነበት ወቅት ላይ በርካቶች ጸረ-ኢትዮጵያ ተብለው ወደ ተለያዩ ማጎሪያ ቤቶች ወርደዋል። ከዚህ በተቃራኒ ደግሞ አማራ እንደሌሎች በብሔሩ ተደራጅቶ መብቱን ካላስከበረ ቀጣዩ ዘመን የውርደት መሆኑን የተረዱ እንደ ፕሮፌሰር አሥራት ያሉ ልሂቃን ህይዎት እስከማጣት ዋጋ ከፍለዋል። የእነ ፕሮፌሰር አሥራት ወቅቱን የዋጀ የፖለቲካ ትግል ቢያካሂዱም የአማራ ሕዝብ እና ልሂቃኑ በተገቢው መንገድ ተረድቶ አልደገፋቸውም ነበር።

## 4. መደምደሚያ

የፖለቲካ ማኅበረሰብ መፍጠር ሀገርን እና ሕዝብን በዘላቂነት ወደ ለውጥ ለመውሰድ አይነተኛ መፍትሄ ነው። የሚታገል፣ በአግባቡ መመራት የሚችል እና መሪ የሚፈጥር ሕዝብ የፖለቲካ ማኅበረሰብ ነው። ኢትዮጵያውያን ደካማ የሆነ የፖለቲካ ባህል ስላለን በተለያየ ማንነት ተከፋፍለን ለሀገራችን በአንድ ላይ መቆም ካቃተን ውለን አድረናል። በዚህ ምክንያት ኢትዮጵያን ከነ አካቴው የሚጠሉ አደረጃጀቶች ወደ ስልጣን መጥተው ሀገርን እና ሕዝብን አደጋ ውስጥ ጥለዋል፣ አሁንም በዚያ ሁኔታ ውስጥ እንገኛለን። በተለይ ደግሞ የአማራ ሕዝብ ከሌሎች ብሄሮች በተለየ መልኩ ስሁት የሆነ ትርክት ተቀርጾለት ለግማሽ ክፍለዘመን ሲጨፈጨፍ ቆይቷል። አንደኛው የብሔር ጽንፈኛ ቡድን ሲወገድ ሌላኛው ተረኛ መጥቶ አማራን በከፋ ደረጃ ለእልቂት እየዳረገ ይገኛል። በአሁኑ ስዓት ሥርዓቱን በአፈሙዝ ለማስወገድ ነፍጥ አንስቶ የሚታገለው የአማራ ሕዝብ ከዚህ በፊት የተሰሩበትን የክፋት ድሮች በመበጣጠስ አንድ የፖለቲካ ማኅበረሰብ መፍጠር የትግሉ ወሳኝ ምዕራፍ ሆኖ እናገኘዋለን። የሕዝቡን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት ብርቱ ሥራ የሚጠይቅ፣ መነሻ እና መዳረሻውን በጥንቃቄ መተንተን የሚገባ ሲሆን ይህን ሀላፊነት የአማራ ፋኖ ሕዝባዊ ድርጅት (አፋሕድ) የመሪነት ሚናው የጎላ ሆኖ እናገኘዋለን።

ድል ለአማራ ሕዝብ!
ሰላም ለኢትዮጵያ!
ረቡዕ መስከረም ፯ ቀን ፳፻፲፰ ዓ.ም.
ኢትዮጵያ።

## The Amhara as a Political Community

(Contiued from page 1)

This movement, led by individuals with anti-Ethiopian sentiments, including Eritreans and members of the Tigray People's Liberation Front (TPLF), systematically vilified the Amhara, and contributed to create a generation gap. Unlike other ethnic groups with organized backing (e.g., TPLF, EPLF, OLF), the Amhara lacked a cohesive strategy, leading to their political

fragmentation. *The central question is whether the Amhara elite have learned from these historical mistakes and established a sustainable organizational framework to address their challenges, or if they risk repeating past errors.*

**2. Challenges in creating a Political Community**

The Amhara face both external and internal obstacles in becoming a cohesive political community:

**2.1. Persistent False Narratives:** Anti-Amhara groups, such as TPLF and OLF, have systematically portrayed the Amhara as oppressors, alienating them from other Ethiopian communities and the international community. This propaganda has justified violence against the Amhara, including ethnic massacres, while discouraging their political organization by labeling it as supremacist. False narratives have also been instilled in younger generations through media, publications, and manipulated education systems, further isolating the Amhara.

**2.2. The Amhara people represented by fake individuals:** Post-1991, under Ethiopia's ethno-linguistic federal system, Amhara leaders appointed to represent the community have often been self-serving and were not originally Amharas. These leaders, aligned with anti-Amhara forces, have suppressed the community's ability to organize and resist. A network of loyalists, including corrupt officials and institutions, has perpetuated this marginalization, stifling the Amhara's political consciousness. To mention some, Bereket Simon, Adisu Legese, Kassa Teklebirhan, Demeke Mekonnen and Helawi Yosef.

**2.3. Internal** Division **among Amhara Forces:** Amhara political groups often engage in infighting rather than collaboration, weakening their collective strength. Debates over whether to pursue civic or ethnic-based politics have divided leaders, while armed groups are further fragmented by regional and local loyalties, hindering the creation of a unified Amhara institution.

**2.4. Over-Reliance on Individual-Led Struggles:** Amhara political efforts are often centered on individuals rather than institutions, making them unsustainable. When key figures are removed or withdraw movements collapse. This reliance on personalities, often tied to local identities, prevents the formation of a robust political community.

**2.5. Emotionalism:** The Amhara's cultural pride and historical legacy are strengths, but the political actions are often driven by emotion rather than strategy. Relying on historical figures or slogans without adapting to current realities undermines effective organization and sustainable progress.

**3. Pathways to Create a Political Community**

**3.1. Studying and Documenting Amhara History:** To counter false narratives, the Amhara must rigorously study and document the history, exposing the origins and impact of anti-Amhara propaganda. This effort is not about fostering resentment but about ensuring accountability, protecting Amhara interests, and educating future generations to learn from past mistakes.

**3.2. Building Institutions:** A political community requires strong institutions with consistent leadership and adaptability to changing circumstances. By drawing on the Amhara's cultural values and learning from global examples of successful ethnic struggles, a robust institutional framework should be established to unify and mobilize the community.

**3.3. Awakening the Elite from Idealism:** The Amhara elite must move beyond idealistic notions of civic politics and recognize the necessity of ethnic-based organization in Ethiopia's current federal system. Leaders like Professor Asrat, who paid the ultimate price for advocating Amhara rights, were not adequately supported. The elite must align with the community's needs to build a cohesive political movement.

**4. Conclusion**

Creating a political community is essential for sustainable change and effective leadership. Ethiopia's weak political culture has allowed divisive forces to exploit ethnic differences, with the Amhara facing unique vilification and marginalization for decades. As new extremist groups continue to target them, the Amhara's armed struggle, led by organizations like the Amhara Fano People's Organization (AFPO), represents a critical step toward forming a political community. This requires strategic planning, historical reflection, and strong institutional frameworks to address the Amhara's challenges and secure their place in Ethiopia's future.

Victory to the Amhara People!
Peace for Ethiopia!
September 17, 2025.

## Notes on Pan Africanism

(continued from Page 1)

But let us be clear: if left solely to the machinery of African governments, Pan-Africanism will remain a dream deferred, likely postponed for yet another generation. History has shown us time and again that the state apparatus is too often consumed with short-term gains, political self-preservation, and fragmented national interests. The real force for the revival of Pan-African ideals will not come from above but from below—from the bold, tech-savvy, and globally aware Generation Z. They possess both the tools and the daring spirit to transform digital spaces into arenas of mobilization and resistance.

Once this rising generation takes ownership of Pan-Africanism and channels its energy into building sustained political pressure, African governments will no longer be able to ignore the call. They will be compelled—by necessity rather than choice—to implement at least some of the movement's long-standing ideals. Chief among these is the African Continental Free Trade Area (AfCFTA), which, if fully realized, will do more than just create a single market for goods and services. It will tear down colonial-era barriers, unleash economic creativity, and lay the material foundation for a more integrated and self-reliant Africa.

Allow me, then, to close this note with a heartfelt salute to our Pan-Africanist brothers and sisters across our vast, diverse, and beautiful continent. Pan-Africanism is not a foreign idea—it is a living pulse within our people, one that beats strongly in Ethiopia and in every corner of Africa where men and women dream of dignity, unity, and freedom. What remains is for us to tap into this abundant reservoir of commitment, courage, and solidarity. Together, we can nurture this cause until it grows into a force too powerful to be ignored, a movement that embodies both the legacy of our ancestors and the aspirations of future generations.

Keep up the good work, brothers. We have nothing to lose but the shackles of colonialism.

## የሳምንቱ ዐበይት ዜናዎች

- **በጦር ሜዳ ብስጭት ውስጥ የሚገኘው አገዛዙ ቤት ማቃጠሉ ተሰማ**

በደቡብ ጎንደር ዞን ታች ጋይንት ወረዳ አርብ ገበያና አጋጥ በሚባሉ ከተሞች የፋኖ ቤተሰቦችን ቤት በማፍረስ ቆርቆሮና የቤት ውስጥ እቃዎችን ማቃጠሉ ታውቋል። ከተቃጠሉት ቤቶች መካከል የአፋሕድ ጎንደር ጠቅላይ ግዛት እዝ 206ኛ ኮርና የገብርየ ክ/ጦር ዋና አዛዥ አርበኛ አዲሱ ደባልቄ እንዲሁም የገብርየ ክ/ጦር ም/ል አዛዥ አርበኛ አዳነ ተስፋና የክፍለጦሩ ዘመቻ የያለው ጥላሁን ቤተሰብ (የአባቱ አቶ ጥላሁን ቤት) ሲገኙበት ቃጠሎውን ያስተባበሩት ጄ/ል መሀመድ ተሰማና የዞኑ ብልፅግና ሀላፊ መንበር ክፈተው የተባሉ የጨፍጫፊው ስርዓት ታማኝ አገልጋዮች ናቸው። ድርጊቱ ግልፅ የጦር ወንጀለኝነት በመሆኑ ይበልጥ አገዛዙን በአንድነት መታገል እንደሚገባ ማሳያ ነው ሲሉ አርበኛ አዲሱ ደባልቄ ገልፀዋል።


በተመሳሳይ ከወር በፊት የአገዛዙ ታማኝ አገልጋዮች የአንበሳው ጋይንት ክጦር አመራር ቤተሰቦችን ቤት በማፍረስ በርካታ ቁሳቁሶችን በመስረቅ የቀረውንም ከጥቅም ውጭ በማድረግ ኅሊናቸው የማይወቅሳቸው የቁስ ሰቀቀናሞች መሆናቸውን ማስመስከራቸው አይዘነጋም።

## Brief News Highlights

- **The regime has continued avenging its losses on civilian properties**

It has been reported that the houses of Fano families in the towns of Arb Gebeya and Agat in the South Gondar Zone of Tach Gayint Woreda were demolished and their roofs and household goods were burned. Among the houses burned were that of the families of commander of 206th Corps, and Gebrye Division of the AFPO Gondar Provincial Command, Adissu Debalkie; that of the Vice-Commander of the Gebriye Division Patriot Adane Tesfa; and that of the father of the Operations Commander of Gebrye Division, Patriot Yalew Tilahun. It has also been learnt that loyal regime servants General Mohammed Tessema and the Zonal PP representative Menber Kifetew led the burning and destruction. Addisu has noted that the fact that the regime routinely engages in war crimes is one more justification to fight against it.

Similarly, it should not be forgotten that a month ago, the loyal servants of the regime demolished the houses of the families of a commander in the Anbessaw Gayint Division, and looted and destroyed belongings – further confirming their moral depravity.







ከላይ የቀጠለ | continued

### ❖ አፋሕድ በሚቆጣጠራቸው አካባቢዎች የ2018 ዓመት ትምህርት ተጀመረ

አፋሕድ በሚቆጣጠራቸው ግዛቶች የ2018 የትምህርት ዘመን መጀመሩን የአፋሕድ የማኅበራዊ ዘርፍ አስተባባሪዎች አስታውቀዋል። ትምህርት የትውልድ መሠረት መሆኑን የሚረዳው አፋሕድ በአንድ እጁ ለጠላት ብልፅግና አፈሙዙን በሌላ እጁ ብዕር ይዞ ትውልድ እንዲማር እየተረባረበ ይገኛል። በዚህም በሚቆጣጠራቸው አካባቢዎች ሰፊ የሕዝብ መድረክ በመፍጠር ተማሪዎች እንዲመዘገቡና እንዲማሩ የቀሰቀሰ ሲሆን የአለማቀፋ ህግጋት በሚፈቅደው መንገድ ለመምህራንና ተማሪዎች



ተገቢ ከለላ በመስጠት ማኅበረሰቡን የማስተባበርና የትምህርት ተቋሙ ሰላማዊ የማስተማር ሥራው እንዲጥል ቃል በገባው መሰረት እየሰራ መሆኑን አስታውቋል።

### ❖ Schools re-open for the 2018 Academic Year in AFPO-controlled areas

The social sector coordinators of the AFPO announced that the 2018 school year has begun in areas under their control. AFPO understands that education is the foundation for a successful generation. As a result, it is working hard to educate the generation with one hand, while fighting the enemy with the other. To that end, it has created a wide public platform in the areas it controls to encourage students to register and learn, and it has announced that it is working as promised to coordinate the public and ensure that the schools continue the teaching-learning process, providing appropriate protection to teachers and students in accordance with International Law.

### ❖ አፋሕድ በጎንደር ጠቅላይ ግዛት እዝ ለሚተዳደሩ አቅመ ደካሞች ድጋፍ አደረገ

ባለፈው ሳምንት በውጭ ሀገር በሚኖሩ ደጋግ ሰዎች በተሰበሰበ ገንዘብ ከ600 በላይ ለሆኑ አባወራዎች የምግብ እህል ገዝቶ ድጋፍ አድርጓል። ድጋፉ የተደረገው ከፍተኛ የምግብ እጥረት በተከሰተበት በላይ ጋይንት ወረዳ ነገላ ዙሪያ ባሉ ቀበሌዎች ሲሆን በድጋፉ ርክክብ ወቅትም የአፋሕድና የ206ኛ ኮር አመራሮች ቦታው ላይ በመገኘት ያስተባበሩ ሲሆን፤ በተጨማሪም በቀጠናውና በአጎራባች ወረዳዎች ሰፊ ቁጥር ያለው ማኅበረሰብ አስቸኳይ የሰብዓዊ እርዳታ ሊደረግለት እንደሚገባ አሳስበዋል።




### ❖ AFPO Gondar Command Distributes Aid to the Vulnerable in areas Under its control

AFPO Gondar Command distributed food relief supplies to more than 600 households with financial support from generous individuals living abroad. The support was provided in the kebeles around Negela in Lay Gayint Woreda, where severe food shortages have occurred. During the support handover, AFPO and 206th Corps leaders were present at the scene to coordinate safe distribution of supplies. On the ocassion, the 206th Corps leaders urged that essential humanitarian assistance be supplied urgently to the large number of families in Kebeles around Negela and neighboring woredas affected by severe drought and subsequent food shortage.

### ❖ አፋሕድ አለማቀፍ የአንድነት ጉባኤ ሊያካሂድ ነው

አፋሕድ መስከረም 10 እና 11 አለማቀፍ ጉባኤ ሊያካሂድ ሲሆን የጉባኤው ዋና አላማም የፋኖ አንድነት እንዲሳካ ምክክር በማድረግ ምቹ ሁኔታን መፍጠር ሲሆን የትግሉን ሁኔታ በተመለከተ እስካሁን የመጣንባቸው መንገዶች፣ አሁን ያለንበት ቁመና እንዲሁም የነገ እጣፈንታችን በተመለከተ ከበርካታ ደጋፊዎችና ባለደርሻ አካላት ጋር ይመክራል።

በጉባኤው መላ የትግሉ ደጋፊ በልዩ ልዩ የሚዲያ አውታሮች እንዲሳተፍ የሚመቻች ሲሆን የአፋብኃ ከፍተኛ አመራሮችም በዚሁ ጉባኤ ጥሪ ተደርጎላቸዋል።




### ❖AFPO to Hold an International Fano Unity Conference

AFPO will hold an international conference focusing on Fano Unity on September 20 and 21. The main objective of the conference is to create a conducive environment for the discussions on the unity of Fano and the path we have come so far, our current position, and our future destiny with many supporters and stakeholders.

The conference will be open to all supporters of the struggle through various media outlets, and senior leaders of the AFNF have also been invited to the conference.

# በምስሎች In Pictures











